# ግብርና ታክስ በግምት ስለመወሰን የወጣ መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# ግብር እና ታክስ በግምት ስለመወሰን
# የወጣ መመሪያ ቁጥር 29/ 2001

ትክክለኛ ገቢን አስታውቆ ግብርና ታክስ መክፈል በግብር ከፋዩ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ሲሆን ይህን ኃላፊነት በማይወጡ ግብር ከፋዮች ላይ የሚፈለግባቸውን ትክክለኛ የግብርና የታክስ መጠን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ፣ ወይም የሂሳብ መዝገቡ እና ሰነዱ ተቀባይነት ሲያጣ፣ ወይም ግብር ከፋዩ ገቢውን ወቅቱን ጠብቆ ያላስታወቀ እንደሆነ በየወቅቱ የሚታየውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የዋጋ ግሽበት ከግምት ውስጥ በማስገባት የግብሩንና የታክሱን ልክ በግምት ለመወሰን እንዲቻል፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 16(3) እና አንቀጽ 39፣ እንዲሁም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 35 እና በተርን-ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀጽ 38 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ግብር እና ታክስ በግምት ስለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 29/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

1. "ግብር ከፋይ" ማለት ግብርና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡
2. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 ላይ የተመለከቱት የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች በሚከፍሉት ማናቸውም ግብርና ታክስ ላይ ነው፡፡

## 4. መርህ

ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን ባለስልጣኑ ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም ግብር ከፋዩ በግብር/ታክስ አዋጆች በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 69፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 29 እና በሌሎችም የታክስ አዋጆችና ደንቦች ላይ በተመለከተው መሠረት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን እና የታክሱን ልክ በግምት ይወስናል፡፡

## 5. በትራንስፖርት ንግድ ላይ ስለሚከፈል ግብር

ጠቅላላ ዓመታዊ የሽያጭ እንቅስቃሴው ከብር 100,000 በላይ የሆነ በትራንስፖርት ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ ሕግ በሚያዘው መሠረት፡-

1. ገቢውን አስታውቆ የሚፈለግበትን ግብር ካልከፈለ፣ ወይም አስታውቆ የከፈለው ግብር በግምት ከሚወሰነው /በሠንጠረዥ 1 ከተመለከተው/ ልክ በታች ከሆነ፣
2. አሽከርካሪዎች እና ረዳቶቻቸው ሊከፍሉት የሚገባውን የስራ ግብር ቀንሶ በየወሩ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ካላደረገ፣ ወይም በየወሩ ቀንሶ ገቢ የሚያደርገው ግብር በግምት ከሚወሰነው /በሠንጠረዥ “1” ከተመለከተው/ልክ አንሶ የተገኘ እንደሆነ፣

ያቀረበው የሂሣብ መግለጫ ወዲያውኑ ተመርምሮ የሂሣብ መዝገቡ ተቀባይነት ሲያጣ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ “1” መሠረት ግብሩን በግምት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 6. በሌሎች የንግድ ስራዎች ላይ የተሰማሩ የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አወሳሰን፤

ከትራንስፖርት ንግድ ስራ በስተቀር በሌሎች የንግድ ስራዎች የተሰማራ የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋይ ግብሩ ወይም ታክሱ በሚከተለው አኳኋን ይወሰናል፡፡

1. ለግብር ወይም ታክስ ውሣኔ መሠረት የሚሆነው የሽያጭ መጠን የሚወሰነው፤

ሀ- ስለ ግብር ከፋዩ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ከሶስተኛ ወገን መረጃ የተገኘ እንደሆነ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ፣ ወይም

ለ- ስለ ግብር ከፋዩ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የግዢ መጠን ከሶስተኛ ወገን መረጃ የተገኘ እንደሆነ የተገኘውን የግዢ መረጃ ያልተጣራ የትርፍ መቶኛን ተጠቅሞ ወደ ሽያጭ ገቢ በመቀየር፣

ሐ- ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ለ) አፈፃፀም የሚከተለውን ቀመር መጠቀም ይቻላል፡፡

$$\text{ሽያጭ} = \frac{\text{ግዥ}}{1 - \text{የትርፍ መጣኔ}}$$

መ. የተሟላ መረጃ ከሶስተኛ ወገን ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ ለግብሩ ወይም ለታክሱ ስሌት መሠረት የሚሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ግብሩ ወይም ታክሱ ከሚከፈልበት የሂሳብ ወር ወይም ዓመት በፊት በነበረው ወር ወይም ዓመት ግብር ከፋዩ ለከፈለው ግብር ወይም ታክስ መሠረት በሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ላይ ወቅታዊ የዋጋ ግሽበት መቶኛ በማከል የሚደረስበት ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ መጠን፣ ወይም

ሠ- በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል ሀ-ሐ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የግብር ከፋዩን ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ለመወሰን ካልተቻለ ግብር የሚወሰንበትን ድርጅት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ በአካል ተገኝቶ በመመልከት ወይም ከድርጅቱ ጋር ተመሳሳይ የንግድ ዓይነት እና ደረጃ ያላቸው 3

ድርጅቶች ያስታወቁትን ገቢ ወይም/ እና እነዚህ ድርጅቶች ለተወሰነባቸው ግብር ወይም ታክስ መሠረት የሆነውን የሽያጭ ገቢ አማካይ በመውሰድ ይሆናል፡፡

ረ. ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሠ) አፈፃፀም የንግድ ሥራ ድርጅት እንቅስቃሴ በአካል ተገኝቶ በሚገመትበት ወቅት የሚከተሉትን ማከናወን ይገባል፡፡

1. የንግድ ሥራው ያለበትን አካባቢ የንግድ እንቅስቃሴ ማገናዘብን፣
2. የድርጅቱ ሠራተኞች ብዛትን፣
3. የድርጅቱን
    - የመብራት፣
    - የውሃ፣
    - የስልክ ፍጆታ
    - የካፒታል ይዞታና አጠቃቀሙን፣
    - የመሳሰሉትን፣

ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መልክ የሚሠራው የግምት ሥራም የሚመለከተው የሥራ ሂደት ባለቤት በሚመድበው ቡድን የሚከናወን ይሆናል፡፡

ሰ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተው የግምት አወሳሰን በተለይ የሽያጭ መጠን ለተጨማሪ እሴት እና ለተርን ኦቨር ታክስ የግምት አወሳሰንም መሠረት በመሆን ያገለግላል፡፡

2. የትርፍ መቶኛ መተመኛ

ከዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ መጠን ላይ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን የሚከተለው የትርፍ መቶኛ መተመኛ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

ሀ- ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 2 የተመለከተው በየስራ ዘርፉ የተቀመጠው የተጣራ የትርፍ መቶኛ፣

ለ- በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተራ ፊደል “ሀ” የተጠቀሰው ሠንጠረዥ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊሻሻል ይችላል፡፡

3. የኤክሳይዝ ታክስ ውሣኔ መሠረት የሚሆነውን የማምረቻ ወጪ በግምት ስለመወሰን

ሀ/ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የማምረቻ ዋጋ እንደመሆኑ ስለ ሽያጭ መጠን ወይም ስለግዢ ዋጋ ወይም በአንቀጽ 6(1) (መ) መሠረት የተገኘውን የሽያጭ መረጃ ለምርቱ መጠን በማካፈል ወይም ወደኋላ ተመልሶ የማስላት ዘዴን በመጠቀም በቅድሚያ ወደ ማምረቻ ዋጋ በመለወጥ ታክሱን መወሰን ይቻላል፡፡

ለ/ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሀ) አፈፃፀም የሚከተለውን ቀመር መጠቀም ይቻላል፡፡

*ቀመር*

$$\text{ማወ} = \frac{\text{ሽዋ}}{(1 + \text{ት}\ \%)\ (1 + \text{ኤታ}\ \%)}$$

$$\text{ኤታ} = \text{ማወ} \times \text{ኤታ}\%$$

*መግለጫ*

ማወ = ማምረቻ ወጪ

ሽዋ = የምርት ነጠላ መሸጫ ዋጋ/ግምት (unit price)

ት% = የተጣራ ትርፍ

ኤታ% = የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ

ኤታ = ተከፋይ ኤክሳይዝ ታክስ

*መረጃ /ምሣሌ*

አንድ ኩንታል ስኳር በማምረቻ ቦታ/መጋዘን ብር 106 ቢሸጥ እና የተጣራ ትርፉ 15% ቢሆን፡

$$\text{ማወ} = \frac{106}{(1 + 15\%)\ (1 + 33\%)}$$

$$\text{ማወ} = \frac{106}{(1.15)\ (1.33)}$$

$$\text{ማወ} = \frac{106}{2.08}$$

$$\text{ማወ} = 50.96$$

$$\text{ኤታ} = \frac{50.96 \times 33}{100} = 16.82$$

በወር የሚፈለገውን የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ለመወሰን የአንድ ኩንታል ኤክሳይዝ ታክስ ወጪን በወር ውስጥ በተመረተው ምርት መጠን በማባዛት የሚደረስበት ስሌት ይሆናል።

## 7. አስተዳደራዊ መቀጫ

1. መዝገብ ባለመያዝ እና ሌሎች አስተዳደራዊ መቀጫዎች በግብር/ታክስ ሕጎች መሠረት ተሰልተው የግብር/ታክስ ውሣኔው አካል ይሆናሉ።
2. የሂሣብ መዝገብ መያዝ ግዴታውን ያልተወጣ ግብር ከፋይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 89(2) መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይጣልበታል።

## 8. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ________________ ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር